# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ

Council of Peace and Unity of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church


"የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው" (፪ ቆሮ ፲፩፡፳፰)

ሐምሌ 29/2002 ዓ ፡ም

## ከኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ የተሰጠ መግለጫ

«ጸልዩ በአንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን = ስለ ቤተ ክርስቲያን ሰላም ጸልዩ»

ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ ታሪኳ፣ ክብሯና አንድነቷ ተጠብቆ የኢትዮጵያ ምእመናን ማዕከል በመሆን ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ስታስታርቅ መኖሯ በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ የታወቀ ነው፤ በዘመናችን ግን በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ምክንያት በቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል የተፈጠረው ልዩነት ለቤተ ክርስቲያን በዓለም ፊት የፊት ሐፍረት ሆኖ መንፈሳዊ ውበቷን ጋርዶታል፤ የቤተ ክርስቲያን ልጆችም የቀደመ ክብሯና አንድነቷ እንዲመለስ በጸሎትና በኀዘን ላይ ናቸው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ ዋና ዓላማ ከሀገር ውጭ እና በሀገር ውስጥ የሚገኙ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች አባቶቻችን ልዩነታቸውን እና የቤተ ክርስቲያንን ችግር በውይይት ለመፍታት እንዲችሉ የሰላምና የአንድነት መድረክ ማመቻቸትና ችግሩ በሰላም እንዲፈታ መሥራት ነው። በመሠረቱ የሰላምና አንድነት ጉባኤው ከማንኛውም አካል ይሁን አድርግ ሳይባል አባቶችን በማቀራረብ ችግሩን በሕይወት እያሉ መፍታት አለብን ብለው የተነሣሱ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ኅብረት ነው።

አብዛኞቹ የጉባኤው አባላት በብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ዕረፍት ምክንያት የተገናኙ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሲሆኑ፣ ማንኛውንም አካል እና ድርጅት ሳይወክሉ በራሳቸው አነሳሽነት ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ለመሥራት ፈቃደኞች የሆኑ ካህናትንና ምእመናንን ያካተተ የሰላም ጉባኤ ነው። ካህናቱ ከልዩ ልዩ አካባቢ የተሰባሰቡ ሲሆኑ ምእመናኑ ደግሞ ከዚህ በፊት ስለ ቤተ ክርስቲያን ሰላም ጥረት ጀምረው የነበሩ ናቸው። የሰላምና የአንድነት ጉባኤው አዲስ አበባ ከሚገኙ አባቶችና በሰሜን አሜሪካ ከሚገኙት አባቶች ዘንድ በግንቦት ወር 2002 ዓ/ም በተካሄደው የርክበ ካህናት ስብሰባ ልዑካንን ልኮና ተጻጽፎ ችግሩን በውይይት ለመፍታት ይቻል ዘንድ ከሁለቱም አስፈላጊውን ፈቃድና እውቅና አግኝቷል። ይህም ማለት ጉባኤው የሰላም ጥረቱን እንዲቀጥል በደብዳቤ ተፈቅዶለታል። ስለዚህ በተገኘው የአባቶች ፈቃድ መሠረት፥ ከሁለቱም አቅጣጫ በሊቃነ ጳጳሳት የሚመሩ ልዑካን የሰላምና የአንድነት ውይይቱን ይጀምሩ ዘንድ የሰላም ጉባኤው የውይይቱን ቀንና ቦታ ወስኖ ስላስታወቀ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ተወክለው ከአዲስ አበባ የተላኩ አራት ልዑካን ለውይይት ወደ ዋሽንግተን ዲሲ የመጡ ሲሆን እነዚህም፦

1) ብፁዕ አቡነ ገሪማ ሊቀ ጳጳስ
2) ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳስ
3) ንቡረ ዕድ ኤልያስ አብርሃ
4) መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ናቸው።

በአንጻሩ ደግሞ በሰሜን አሜሪካ ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርርስቲያ ቅዱስ ሲኖዶስም የተወከሉ አራት ልዑካን ለውይይት ዋሽንግተን ዲሲ ገብተዋል። እነዚህም፦



P. O. BOX 505, Stone Mountain, GA 30086 E-mail: copauoeotc@yahoo.com

1) ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ
2) ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ሊቀ ጳጳስ
3) ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ
4) መልአከ ገነት ገዛኸኝ ገብረ ክርስቶስ ናቸው።

ጉባኤውን ለማካሄድ የሰላምና አንድነት ጉባኤው ከፍተኛ ወጭ አውጥቶ ደረጃውን የጠበቀ ከፍተኛ ዝግጅት አድርጎአል። ከሐምሌ 26-29 2002(Augst 2-5/2010) በ Hilton McLean Tysons Corner 7920 Jones Branch DR Virginia 22102፥ ስብሰባውን አካሂዶአል፣ ነገር ግን ልዑካኑ ፊት ለፊት በጠረጴዛ ዙሪያ ውይይቱን ማካሄድ ባለመቻላቸው የታሰበው ውይይት በሰላምና አንድነት ጉባኤው አባላት አማካይነት ንግግሩ(proxy talk) ተካሂዶአል። በመሠረቱ ፊት ለፊት ቀርቦ ለመነጋገር ያለስቻለው ዕንቅፋት በሰሜን አሜሪካ ባሉት አባቶች በኩል የተላኩ ልዑካን ለሰላምና አንድነት ጉባኤው ቀደም ሲል ያቀረቡት ጥያቄ መልስ ስላላገኘ ነበር፣ ይህም ጥያቄ ከአዲስ አበባ ከተመደቡት ልዑካን መካከል በአንዱ ላይ ከፍተኛ ቅሬታ ስለነበራቸውና ልዑኩ «በእኛ ላይ ትክክለኛ ያልሆነ መግለጫ ያስተላለፉና የቤተክርስቲያንን ታሪክ የሚያዛባ ትምህርት የሰጡ በመሆኑ ከእርሳቸው ጋር በጉባኤ ስለማንቀመጥ ከልዑካኑ ውስጥ እንዳይገቡ » ብለው ስላሳሰቡ፣ የሰላም ጉባኤውም ግለሰቡን ከልዑካን መካከል እንዳይሆኑ በደብዳቤም ሆነ በስልክ ያደረገው ጥረት ስላተሳካ ነው።

ከዚያም ልዑካኑ ከተመደቡ በኋላም ወደ ዋናው ስብሰባ ሳንደርስ የሰላምና አንድነት ጉባኤው ቃል በገባው መሠረት በቅድሚያ ለማግባባት ያደረግነው ጥረት ከአዲስ አበባ በመጡት ልዑካን በኩል ተቀባይነት ማጣቱና የሰላምና አንድነት ጉባኤውም ለሰላምና ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ከነበረው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ እናስፈጽመዋለን ያለውን ቃል ለማስፈጸም ያደረገው ጥረት ባለመሳካቱ ነበር። ይህ በዚህ እንዳለ ለሁለቱም ልዑካን ጉዳዩ ከአቅም በላይ መሆኑን በገለጽንበት ጊዜ በውጭ ሀገር ባሉ አባቶች ልዑካን በኩል «ሦስት ለሦስት እንወያይ» እንዲሁም በሰላምና አንድነት ጉባኤውም አባላት በኩሉ «በሊቃነ ጳጳሳት ደረጃ ብቻ ሁለት ለሁለት ውይይቱ ቢካሄድ» የሚል አማራጭ ሐሳብ አቅርቦ ነበር ። ነገር ግን የአዲስ አበባው ልዑካን «ይህ ከመመሪያ ውጭ ያደርገናል» ስላሉ ሳይሳካ ቀርቷል። በመጨረሻም ሁለቱም ልዑካን ችግሩን አቅርበንላችው የሐሳብ ለውጥ ለማድረግ ባለመስማማታቸው ምክንያት ሁለቱም ልዑካን በሰላም ኮሚቴው አማካይነት ባደረጉት ንግር(proxy talk) የሰላሙ ውይይት በሚቀጥሉት ሦስት ወራት ውስጥ ለዚህ ጉባኤ ስኬታማነት እንቅፋት የሆነው ችግር ተስተካክሎ ተለዋጭ ስብስባ እንዲረግ ሰምምነት ላይ ደርሰዋል። ከዚህም ጋር ሁለቱም ልዑካን በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ተስማምተዋል።

1) ከ3-4 ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ ተለዋጭ ጉባኤ እንዲካሄድ፤
2) የሰላምና አንድነቱን ጥረት የሚያሰናክሉ ማንኛቸውንም ነገሮች በቃልም ሆነ በጽሑፍ እንዳይተላለፍ ፤
3) የሰላምና አንድነት ጉባኤው የጀመረውን ከፍተኛ ጥረት እንዲቀጥል፤
4) ለተጀመረው የሰላምና አንድነት ጥረት ስኬታማነት አስፈላጊውን ትብብር ለሰላምና አንድነት ጉባኤው ሊደርጉ ፈቃዳቸውን ገልጠዋል።

ይሁን እንጅ በሰላምና አንድነት ጉባኤው ከተደከመው ድካምና ከተከፈለው መስዋዕትነት አንጻር ያስገኘው ውጤት በዓለም ዙሪያ የሚገኙና የቤተ ክርስቲያንን አንድነትን የሚናፍቁትን ካህናትና ምእመናን ጥያቄ የሚመልስ ባይሆንም፥ ለ18 ዓመታት የቆየው ችግር በአንድ ስብሰባ ሊፈታ እንደማይችል የሰላም ጉባኤው ተገንዝቧል። ለወደፊቱም ጉባኤው ጥረቱን አጠናክሮ ለመቀጠል ለሁለተኛው ዙር ስብሰባ ከወዲሁ ዝግጅቱን ጀምሯል።

*በመሆኑም የሰላምና አንድነት ጉባኤው አቋም፦*

1) *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንድነትና ሰላም ለሀገራችን ሰላምና አንድነት መሠረት መሆኑን ፍጹም ያምናል። የቤተ ክርስቲያን አባቶች ልዩነት የቤተ ክርስቲያናችንንና የሀገራችንን የኢትዮጵያ አንድነትና ሕልውና ለማይፈልጉም ትልቅ በር ከፍቶላቸዋል። ይህም ዐቢይ ችግር የቤተክርስቲያንን አንድነት በማጽናት ሊገታ ይገባዋል።*
2) *ጥንታዊትና ሐዋርያዊት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዘመናችን ከሁለት ከሦስት ተከፍላ ልጆቿም እንደ ባለ ደም ማዶ ለማዶ የሚተያዩ ሆነዋል። ይህም የቤተ ክርስቲያኒቱን የረጅም ዘመን ታሪክና መንፈሳዊ አቋም አዛብቷል፤ በልጆቿም መካከል ፍቅርን እያጠፋና ኃይሏን እያዳከመ ይገኛል። ይህን ለማቆም የቤተ ክርስቲያን አንድነት አስፈላጊ መሆኑን ያምናል፤*
3) *የቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት እስኪመጣ ድረስ የሰላምና አንድነት ጉባኤው ጥረቱን የሚቀጥል መሆኑን ይገልጻል፤*
4) *በዓለም ዙሪያ የሚገኙ የቤተክርስቲያንን ሰላምና አንድነት የሚናፍቁ ሁሉ በጸሎት በሐሳብና አቅምን በማጠናከር እንዲያግዙት ይጠይቃል፤*
5) *ይህ የሰላምና አንድነት ጉባኤ ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ነጻና ማንም የማይጠቀምበት ነገር ግን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት የሚሠራ የሰላምና አንድነት ጉባኤ ነው።*
6) *በአባቶች መካከል የተፈጠረው መለያየት፣ ከሁለቱም አቅጣጫ የተላለፈው ውግዘት፣ በዜና አውታሮች የሚሰማውና በድኅረ ገጾች የሚነበበው መነቃቀፍ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ልጆች መንፈሳዊ ስሜት እጅጉን ጎድቶአል። ስለዚህ ይህን መነቃቀፍ የሚያቆመው የቤተ ክርስቲያን አንድነት መሆኑን የሰላም ጉባኤው ያምናል።*
7) *የሰላምና አንድነት ጉባኤው የሚያደርገውን የሰላምና አንድነት ጥረት ለማሰናከል ከየአቅጣጫው የሚሰነዘሩትንና ከጉባኤው ዓላማ ውጭ የሆኑ የተሳሳቱ መልእክቶችን በመመከት ወደፊት አስፈላጊውን መረጃ እየሰጠ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት መሥራቱን የሚቀጥል መሆኑን እንገልጣለን።*

*በመጨረሻም ይህን የመሰለው ታላቅ መንፈሳዊ ሥራ በበጎ ኅሊናና በፈቃደ እግዚአብሔር የሚከናወን በመሆኑ እግዚአብሔር ሕዝባችንን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አንድ በማድረግ ይባርክ ዘንድ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ሰላምና አንድነት ጸልዩ። ወደ እግዚአብሔርም በጸሎት የቤተ ክርስቲያናችንን ችግር አቅርቡልን። የጉባኤውም የሰላም ጥረት ግቡን እንዲመታና የተፈጠረው ችግር በውይይት ተፈቶ ለትውልድ አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለማስረከብ እንድንችል ተግታችሁ ትጸልዩልን ዘንድ በትሕትና እንማጸናችኋለን።*

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ*
*እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።*

